# የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
## የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር
# Federal Democratic Republic of Ethiopia
## MINISTRY OF FOREIGN AFFAIRS


ቀን 13 ጥቅምት 2010
Date

ቁጥር ... 31/11/10
No.

**ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሚሲዮኖች/ቆንስላ ጄኔራል/ ቋሚ መልዕክተኛ/ንግድ ጽ/ቤቶች**

**በያሉበት**

የትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በክልሉ 12 ታላላቅ ከተሞች ተግባራዊ የሚሆንና ታህሳስ ወር 2009 ዓ.ም. ያወጣውን ራስ አገዝ የመኖሪያ ቤቶች ህብረት ስራ ማህበር ማስፈፀሚያ ማንዋል ይዘት የሚጠቁሙ ዋና ዋና ነጥቦችን ከትግርኛ ወደ አማርኛ ቋንቋ በመተርጎም ከማስፈፀሚያ ማንዋሉ ሙሉ ትግርኛ ቅጂ ጋር ስንልክ በፕሮግራሙ ተጠቃሚ ለመሆን የሚፈልጉ የዳያስፖራ አባላት በባንክ በውጭ ምንዛሪ ለመኖሪያ ቤቱ መስሪያ የሚሆን ግምት ገንዘብ ማስቀመጥና ገንዘቡ ገቢ የተደረገበትን ማስረጃ ማቅረብ እንደሚያስፈልግ ማሳወቃችን ይታወሳል::

ሆኖም ግን አንዳንድ የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት አባላት ለመኖሪያ ቤቱ ግንባታ ወጪ ክፍያ በግላቸው የከፈቱት የዳያስፖራ አካውንት ውስጥ ያስገቡት ገንዘብ በማህበሩ ስም ወደተከፈተው አካውንት ሊገባላቸው አለመቻሉን ጠቅሰው ድጋፍ እንድናደርግላቸው እንደሚጠይቁ ተገንዝበናል::

ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው ለመኖሪያ ቤት መስሪያ የሚሆን ግምት ገንዘብ በውጭ ምንዛሪ ማስቀመጥ እንደሚያስፈልግ ቀደም ሲል ለሁሉም ሚሲዮኖች ባስተላለፍነው ሰርኩላር መግለጻችንን እያስታወስን፣ ያጋጠመውን ችግር አስመልክቶ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ጋር ባደረግነው ውይይት የዳያስፖራ አባላት በአገር ውስጥ ባንኮች እንዲከፍቱ ከሚፈቀድላቸው ሶስት አይነት የዳያስፖራ አካውንቶች መካከል ወደ ብር የሚቀየረው (Non-rapatriable Birr Account) እና የጊዜ ገደብ (Fixed Time Deposit) የዳያስፖራ አካውንቶች ወለድ የሚታሰብላቸው ናቸው:: በሌላ በኩል ለመኖሪያ ቤቱ መስሪያ አካውንት ውስጥ እንዲገባ የሚጠበቀው ገንዘብ ደግሞ ከወለድ ጋር ግንኙነት የሌለው የቤት ዋጋ ግምት ብቻ መሆን እንደሚገባና ይህም ወለድ የማይታሰብለት ተንቀሳቃሽ ሂሳብ (Current Account) መሆን እንደሚኖርበት የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አሳውቋል:: ከላይ የተጠቀሱት ማነቆዎች የተፈጠሩት አባላቱ የተለያየ አይነት የዳያስፖራ አካውንት በመክፈታቸው እንደሆነ ለመገንዘብ ተችሏል::

ስለሆነም የሚደራጁ የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት አባላት ለቤቱ ግምት የተቀመጠውን ገንዘብ ወጥነት ባለው መልኩ በውጭ ምንዛሪ ተንቀሳቃሽ ሂሳብ (Current Account) ማስቀመጥ የሚገባቸው መሆኑ ታውቆ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ማህበራትና አባሎቻቸው ይህንኑ በእናንተ በኩል እንዲያውቁት እንዲደረግ እንጠይቃለን::

ከሠላምታ ጋር

ደመቀ አጥናፉ
ዳይሬክተር ጄኔራል
የዳያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች
ዳይሬክቶሬት ጄኔራል

ግልባጭ:- ለክቡር ሚኒስትር ዴኤታ ጽ/ቤት (ቢዝነስና ዳያስፖራ ዘርፍ)
ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር
አዲስ አበባ